# የኢትዮጵያን ፈጣን እድገት ማደናቀፍ አይቻልም

ሂለን ኢፕስታየን ሜይ 2010 የዓለም ባንክ ለኢትዮጵያ ህዝብና መንግሥት የሚያደርገውን የገንዘብ ድጋፍ በመቃወም ፅሁፍ አውጥተዋል፡፡ ይህንኑ የፀኃፊዋን አስተያየት በመቃወም በዓለም ባንክ የኢትዮጵያና የሱዳን ዳይሬክተር የሆኑት ኬን ኦህሺ፣ና በዓለም ባንክ ከፍተኛ የምጣኔ ሀብት ባለሙያ ሻንታ ደቨርጃን የሰጡት ምላሽ ከድረ ገፅ ላይ ስላገኘሁት አብዛኛው አማርኛ እንባቢ እውነታውን ይረዳው ዘንድ እንደሚከተለው ጠቅለል አድርጌ አቅርቤዋለሁ፡፡

ለታዳጊ ሀገሮች ልማት የሚደረግ ዕርዳታ ወይም ድጋፍ ሁለት ዓላማዎችን መሰረት አድርጎ የተቀረፀ ነው። እነርሱም፤ የሃገራትን ዕድገት ማፋጠንና በህዝብ ላይ የተንሰራፋውን ድህነት መቀነስ ተቀዳሚ ዓላማዎቹ ናቸው፡፡ ከዚህ አነፃር ጉዳዩን ስንመረምረው ኢትዮጵያ ከ2003 ዓ.ም ጀምሮ ፈጣን፣ አስተማማኝና ቀጣይነት ያለው የኢኮኖሚ ዕድገት በማስመዝገብና ዓለም በኢኮኖሚ ቀውስ ሲናጥ በነበረበት ወቅት እንኳን ኢትዮጵያ በአስገራሚ ሁናቴ እድገት እስመዝግባለች ይላሉ ኦህሺ።

ኦህሺ ፁሁፋቸውን በመቀጠልም የተባበሩት መንግስታት የልማት ፕሮግራም (UNDP) ባውጣው 2009 ሪፖርት ላይ ኢትዮጵያ ሂዩማን ዴቨሎፕመንት ኢንዴክስ (HDI) ያሳየችው እድገት ከአጠቃላይ የዓለም ሀገራት ጋር ሲነፃፀር ከፍተኛ ለውጥ ካስመዘቡ ሀገራት መካከል ከቀዳሚዎቹ ተርታ ያስቀምጣታል። የዘርፉ በለሙያዎች እንደሚናገሩት HDI ለእድገት መለኪያነት ከሌሎች መመዘኛዎች የተሻለ እንደሆነ ይናገራሉ። ምክንያቱም HDI

ሶስት ነገሮችን ማለትም የዜጎችን የእድሜና የጤንነት ሁኔታ፣ ወደ ትምህርት ቤት የሚሄዱ ህፃናት ቁጥርና የጎልማሶች የትምህርት ሁናቴና የህዝብ የአኗኗርና የመግዛት አቅም አጣምሮ በአንዴ ማሳየት የሚችል በመሆኑ ነው። በዚህ መለኪያ ኢትዮጵያ ከፍተኛ እመርታ እንዳሳየች UNDP 2009 ባውጣው ሪፖርቱ ላይ በግልጽ አስቀምጧታል።

በአሁኑ ሰዓት ይላሉ ኬን ኦሀሺ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ያገኘውን የሚሊኒየሙን የልማት ግብ (MDG) ከማሳካት አኳያ ኢትዮጵያ በሁሉም የልማት ዘርፎች ስኬታማ ውጤት በማስመዝገብ ላይ ትገኛለች፡፡ ኢትዮጵያ የከፋ ድህነትንና ረሀብን ከመቀነስ፣ መሠረታዊ ትህምርትን ለዜጐች ከማዳረስ፣ ኤች አይ ቪ ኤድስን ከመከላከልና ከመቆጣጠር፣ ወባን፣ የሳንባ ነቀርሳንና ሌሎች ተዛዳኝ በሽታዎችን ከመከላከል ወዘተ አንፃር ያቀደቻቸውን ግቦች ተግባራዊ በማድረግ በትክክለኛ ጉዞ ላይ የምትገኝ ታዳጊ ሀገር ናት፡፡ የህፃናት ሞትን ከመቀነስና ቀጣይነት ባለው ሁኔታ የአካባቢ ጥበቃን አጠናክሮ ከመቀጠል አኳያም አጥጋቢ ውጤቶችን ከማስመዝገቧ ባሻገር ይህ ተግባር በከፍተኛ ደረጃ ተጠናክሮ ቀጥሏል፡፡

ኢትዮጵያ ሥርዓተ ፆታን ከማስፈንና የሴቶችን እኩልነት በህገመንግሥቷ ከማስፀደቅ ጀምሮ ተግባራዊ እስከማድረግ ድረስ በርካታ አጥጋቢ ውጤቶችን ያስመዘገበች ሀገር ስትሆን በ2015 በመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት ውስጥ ያለውን የፆታ አለመመጣጠን በከፍተኛ ደረጃ እንደምትቀንስ ይጠበቃል፡፡ ለዚህም የፆታ እኩልነትን ለማስጠበቅ፣ የሴቶችን አቅም ለመገንባትና የእናቶችን ጤንነት ለመጠበቅ ያደረገችውና እያደረገችው ያለው ጥረት በከፍተኛ ደረጃ ሊበረታታ የሚገባው አቢይ ተግባር ነው። እነዚህ ከላይ በጣም ባጭሩ የጠቀስኳቸው በአገሪቱ የተመዘገቡ የልማት ስኬቶች ማለትም በአገሪቱ እየተከናወነ

ያለውን አጠቃላይ ብሔራዊ እድገትን የማፋጠንና ድህነትን የመቀነስ ስትራቴጂ እስከዛሬ በዓለም ባንክ በኩል ለተደረጉ ድጋፎች በዋናነት እንደመስፈርት የተጠቀምንባቸው አበይት ተግባራት ናቸው፡፡ ይህም በህዝቡና በአጠቃላይ ሀገሪቱ ላይ ያመጣው ለውጥ በቀላሉ የሚታይ እንዳልሆነ ለመገንዘብ ችያለሁ በማለት ዳይሬክተሩ ይናገራሉ፡፡

ይህ ብቻም አይደለም ይላሉ ኬን ኦሀሺ ፅሁፋቸውን ሲቀጥሉ ሀገሪቱን በመምራት ላይ ያለው መንግሥት በተጨባጭ ላስመዘገባቸው ስኬቶች በተለይም የመንገድ ግንባታና የኤሌክትሪክ ኃይል ልማትና ስርጭት በአበይትነት ሊጠቀሱ የሚገባቸው የልማት ተግባራት ናቸው፡፡ እርዳታና ብድር የምንሰጠው እነዚህ የመሰረተ ልማት ግንባታ ስኬቶች በተከታታይነት በመመዝገብ ላይ ላለው ፈጣን የምጣኔ ሀብት ዕድገት የጀርባ አጥንት በመሆናቸውና ለእድገቱ ተጨባጭ ማስረጃዎች መሆናቸው ነው፡፡ ይህም የሀገሪቱ መንግሥት ለልማት ያለውን ቁርጠኝነት እና ተነሳሽነት በጉልህ ያሳየ አበረታች ተግባር ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ምንም እንኳን ከላይ የተገለፁት በጣም አስፈላጊ የልማት ስኬቶች ቢሆኑም በምናከናውናቸው ተግባራትና በምናደርገው ድጋፍ እነዚህን ብቻ በቂ ናቸው ብለን አልወሰድናቸውም፡፡ በየትኛውም አገር እንደሚታየው ልማት የነዚህ እንቅስቃሴዎች ብቻ ውጤት አይደለም፡፡ ልማት ከእነዚህም ባሻገር የእያንዳንዱን ዜጋ ነፃነትና ዜጎች ያላቸውን ዕምቅ ሀብት ሁሉ ይመለከታል፡፡ ሂለን ኤፐስታየን እንደጠቀሱት ሳይሆን፣ የሀገሪቱ መንግሥት ያለውን የማስፈፀም ብቃት፣ ፍትሀዊ የሀብት ሥርጭትና አጠቃቀም፣ በጥገኝነት ላይ ያለውን አመለካከትና መሠረታዊ የሰብአዊ መብት አያያዝን ሁሉ ተመልክተን ነው ለኢትዮጵያ ብድርና እርዳታ ልንሰጥ የቻልነው እንጂ በዘፈቀደ አይደለም ይላሉ ኦሀሺ ፡፡

ኦሀሺ በመቀጠልም ለሄለን ኤፕስታየን ላረጋግጥላቸው የምፈልገው አብይ ቁም ነገር ቢኖር ብድርና እርዳታን ከመለገሳችን በፊት እነዚህን ሁሉ ፈትሸናል፤ በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ የልማት አጋሮችም በዚሁ መሠረት ተንቀሳቅሰዋል፡፡ እርዳታውን ለመለገስ ከመነሳታችን በፊት በመርህ ደረጃ ይዘን የነበረው የመነሻ ሀሳብ "በማንኛውም ሀገር የሚገኙ ዜጐች ራስን መቻልና መበልፀግን፣ ግልፅነትን፣ ተጠያቂነትን፣ ውጤታማነትን እንዲሁም ልማታዊ የመንግሥት ሥርዓትን ይፈልጋሉ"፡፡ የሚል ሲሆን ኢትዮጵያንም ከዚህ የተለየች ሀገር ሆና አላገኘናትም፡፡ በመሆኑም እንደአንድ የውጭ የልማት አጋር የኛ ኃላፊነት ይህንኑ መደገፍ ነበርና እነዚህ ሀገር በቀል ስኬቶች ተጠናክረው ይቀጥሉ ዘንድ ማድረግ ያለብንን ሁሉ አድርገናል፤ ተገቢም ነው ብለን እናምናለን፡፡

እነዚህ እንዳሉ ሆነው ይላሉ ኬን ኦሀሺ የሚፈለገውን ውጤት ሁሉ በአንድ ጊዜ ያመጣሉ የሚል እምነት የለንም፡፡ ብልፅግና በአንድ ጀንበር ይመጣል ብለን የምናምን የዋሆች አይደለንም። ነገር ግን ተስፋ ሰጪ ጅምሮችን ማጠናከር እንዳለብን ይሰማናል። የልማትም ሆነ የዴሞክራሲ ተቋማትን መገንባትና የህዝብን ተጠቃሚነት ሙሉ ለሙሉ ማረጋገጥ ረጅም ጊዜ እንደሚጠይቅ ይታወቃል፡፡ በበለፀጉት አገሮችም እንደምናየው እነዚህን የህዝብ መሠረታዊ ፍላጐቶች የመገንባት ጥረቶች በሂደት ላይ መሆናቸውን እንጂ በበቂ ሁኔታ ተሟልተዋል የተባለበት ጊዜ መኖሩን አልተመለከትንም፡፡ ለውጥ ወይም የለውጥ ሂደት በተለይም ከድህነትና ኋላቀርነት ጋር ሲያያዝ እየጨመረ እና እየተወሳሰበ የሚሄድ እንጂ በጊዜ ተገድቦ የሚቆም ጉዳይ አይደለም፡፡ ሂደቱም በተለያዩ ጊዜያት በርካታ ፈታኝ እንቅፋቶች ሊያጋጥሙት ይችላሉ፡፡ በመሆኑም በግልፅ እንደሚታወቀው ይህንን ችግር ለመቋቋም ይቻል ዘንድ የልማት አጋሮች የረጅም ጊዜ እቅድ በማውጣት ከሀገሮች ጋር

አብሮ መስራት፣ አስፈላጊውን ድጋፍ ማድረግና ሀገራት ካለባቸው ችግሮች ለመላቀቅና ለማደግ የሚያደርጉትን ጥረት ማበረታታት ይጠበቅባቸዋል፡፡

በርግጥ ይላሉ ኦሀሺ፣  ሄለን ኤፐስታየን እንደገለፁት ለነዚህ ሀገሮች የምናደርገው ዕርዳታ የራሱ የሆነ አሉታዊ ተፅእኖ የለውም ማለት አይደለም፡፡ ይህንን በሚገባ እናውቃለን፡፡ በዚህም ምክንያት ነው ዕርዳታ በምንሰጣቸው ሀገሮች ላይ የቅርብ ክትትል፣ ተከታታይ ምዘናና ከየሀገሪቱ የመንግሥት ኃላፊዎች ጋር በልማቱ ሂደት ላይ ያላቋረጠ ውይይት የምናደርገው፡፡

በአጠቃላይ ፀሀፊዋ እንዳሉት ሳይሆን በኛ በኩል ያለው የአሰራር ሂደት ባጭሩ ይህን የሚመስል ሲሆን ወደፊትም ለኢትዮጵያ የምናደርገው ድጋፍ በዚሁ  መሠረት የሚቀጥል መሆኑን ላረጋግጥ እወዳለሁ  በማለት ኬን ኦሀሺ ሀሳባቸውን ደምድመዋል፡፡

በዓለም ባንክ ከፍተኛ የምጣኔ ሀብት ባለሙያ የሆኑት ሻንታ ደቨርጃን በበኩላቸው “ሰም፣ ወርቅና ተጠያቂነት በኢትዮጵያ” በሚል ርዕስ ባወጡት ፅሁፍ የሚከተለውን አስፍረዋል፡፡ በባልደረባዬ ኦሀሺና በሄለን በኢፐስታየን መካከል የተደረገውን ምልልስ አንብቤያለሁ፡፡ ኤፐስታየን ለመከራከሪያነት ያቀረቡዋቸውን ነጥቦች ማለትም በእርዳታ፣ ድጋፍና በፖለቲካዊ አሰራር መካከል ያለውን ልዩነትም ለመመርመር ሞክሬያለሁ፡፡

ለምሳሌ ያህል ፖለቲካዊ ግልፅነት የሰፈነባቸው ሀገራት እንኳ ለደሀው የህብረተሰብ ክፍል መሠረታዊ ፍላጐቱን ለማዳረስ ባለመቻላቸው ችግር ሲያጋጥማቸው እንመለከታለን፡፡ ለዚህም ጥሩ ማሳያ ህንድን መጥቀሱ በቂ ነው፡፡ በአሁኑ ሰዓት በህንድ የህዝብ ትምህርት ቤቶች የመምህራንን ሽፋን ስንመለከት 25 በመቶ ሲሆን፣ የሀኪሞች ሽፋን ደግሞ 40

በመቶ ብቻ ነው፡፡ ከዚህ ተቃራኒ በሆነ መልኩ “አንዳንድ የፖለቲካ ጭቆና ያለባቸው ሀገራት ድህነትንና በሽታን በፍጥነት ለመቀነስ ችለዋል፤ ለዚህም ኩባና ቻይና ተጠቃሽ ናቸው” በማለት የኤፕስታን ሀሳብ ትክክል እንዳልሆነ ያስረዳሉ።

እዚህ ላይ ድህነትን ለማስወገድ በሚነደፍ ስትራቴጂ  ግልፅ የሆነ ልዩነትን ማስቀመጥ ሊያስቸግር ይችላል፡፡ ይህን ስንል የህብረተሰቡን መሠረታዊ ፍላጐት ማለትም ጤና፣ ትምህርትና የመሳሰሉትን ለማስፋፋትና ለማፋጠን የሚንቀሳቀሰው አካል የፖለቲካ ቁርጠኝነትና ተጠያቂነት ሊኖረው ይገባል፡፡ ይህም በሁለት መልኩ ሊገልፅ ይችላል፤ በፖሊሲ አውጪው ተጠያቂ መሆንና በተጠቃሚው ህብረተሰብ  በኩል ተጠያቂ መሆን ይላሉ ሻንታ ደቨርጀን ፡፡

ደቨርጀን በመቀጠልም በነዚህ ከላይ በሰፈሩት መሰረተ ሀሳቦች ከተስማማን የየሀገራቱን ስኬቶች ስንመረምር ኢትዮጵያን ከሌሎች ሀገራት የተሻለ ሰርታ እናገኛታለን፡፡ በተለይም ድህነትንና የህፃናትን ሞት በመቀነስ፣ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርትን በማስፋፋትና የሴት ተማሪዎችን ቁጥር በመጨመር ያደረገቻቸው እንቅስቃሴዎች በዋቢነት ሊጠቀሱ የሚችሉ ስኬቶች ናቸው፡፡

ይህም ሊሆን የቻለው አስፈፃሚዎቹ አካላት ካላቸው የልማት ቁርጠኝነት ባሻገር ባለባቸው ህዝባዊ ተጠያቂነትም ጭምር ነው፡፡ በአሁኑ ሰዓት ተጠያቂነት ያለበት የአሰራር ስረዕት ተዘርግቶ በመላ ሃገሪቱ ተግባራዊ መሆኑንም በግልፅ አውቃለሁ በማለት ደቨርጀን ሀሳባቸውን ይቀጥላሉ።ለምሳሌ  በወረዳ ደረጃ የሚገኘው የህብረተሰብ ክፍል ፍትሀዊ የሆነ የሀብት ክፍፍል ሲያደርግ ማየት በኢትዮጵያ ውስጥ አዲስ አይደለም፡፡ ይህም መረጃን

መሠረት ያደረገና በሶስተኛ ወገን ሊጣራ የሚችል አሰራርን የተከተለ ግልፅ የሆነ የአሰራር ሂደት ነው፡፡ ይህ ፍትሀዊ አሰራር ተግባራዊ ከመደረጉ በፊት ከህብረተሰቡ ጋር በጋራ በመሆን በስብሰባ የሚወሰን ሲሆን አጠቃላይ ውሣኔያቸውም ሆነ የአሰራር ሂደቱ በግልፅ ለህዝብ እይታ በማስታወቂያ ሰሌዳ ላይ ይለጠፋል፡፡ ይህ አሠራር በዕርዳታ ሰጪው አካልም የተደገፈ በጋራ ግንዛቤ ላይ የተመሠረተ አሰራር እንደሆነ አውቃለሁ፡፡ ይህም የሆነበት አቢይ ምክንያት ከሌሎች ሀገራት ተሞክሮዎች ታይቶ ውጤታማ ሆኖ በመገኘቱና አንዱ የመከታተያ ዘዴም በመሆኑ ነው፡፡